

# FoodShare አባላት፡-

## ከኪስዎ የሚከፍሉት የህክምና ወጪዎች ካሉዎት፣ ተጨማሪ የFoodShare ጥቅማጥቅሞችን ማግኘት ይችሉ ይሆናል።

(FoodShare Members: You may be able to get more FoodShare benefits if you have medical expenses that you pay out of your own pocket.)

- ☐ የFoodShare ጥቅማጥቅሞችን እያገኙ ነው?
- ☐ እድሜዎ ከ 60 በላይ ነው፣ ማየት የተሳነዎት፣ ወይም የአካል ጉዳተኛ ኖት?
- ☐ ከኪስዎ አውጥተው የሚከፍሉት የሜዲካል ወጪ አለብዎት?

**ለሦስቱም ጥያቄዎች "አዎ" ብለው ከመለሱ፣ ተጨማሪ የFoodShare ጥቅማጥቅሞችን ማግኘት ይችሉ ይሆናል።** ይህ የሆነበት ምክንያት ለአንዳንድ የሕክምና ወጪዎች ለሚያወጡት የተወሰነ ገንዘብ ክሬዲት ሊያገኙ ስለሚችሉ ነው። ይህም የሕክምና ወጪ ቅነሳ በመባል ነው የሚታወቀው።

## የሕክምና ወጪ ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-



**በሐኪም የታዘዙ መድሃኒቶች**



**ያለሐኪም የሚገዙ መድኃኒቶች**



**ኢንሹራንስ ፕሪሚየም**



**የዓይን መነፅር እና የመገናኛ ሌንሶች**

## ተጨማሪ ያግኙ፡-

የተወሰኑ የሕክምና ወጪዎችን በማሳወቅ ተጨማሪ የFoodShare ጥቅማጥቅሞችን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ለማወቅ የአካባቢዎትን ኤጀንሲ በስልክ፣ በፖስታ፣ በፋክስ ወይም በአካል ያነጋግሩ። **dhs.wi.gov/forwardhealth/imagency/index.htm በመጎብኘት የአካባቢዎን ኤጀንሲ ማግኘት ይችላሉ።**

የሕክምና ወጪ ተቀናሾች እንዴት እንደሚሠሩ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ሙሉውን መመሪያ በመስመር ላይ በ **www.dhs.wisconsin.gov/publications/p03315b.pdf** ይመልከቱ.

**የFoodShare ጥቅማጥቅሞችን እያገኙ አይደለም?** ለማምለከት አራት መንገዶች አሉ፡-

**በኦንላይን።** በ **access.wi.gov** በኩል በ ACCESS ዌብሳይት ላይ ያመልክቱ።
**በስልክ።** በስልክ በኩል ለማመልከት፣ ለአካባቢዎ ኤጀንሲ ይደውሉ።

**በኢሜል ወይም በፋክስ።** በሚይል ወይም በፋክስ ለማመልከት፣ የተሟላ ማመልከቻ ለአካባቢዎ ኤጃንሲ ይላኩ።

**በአካል።** በአካል ለማመልከት የአካባቢዎን ኤጀንሲ ይጎብኙ። ቀጠሮ መያዝ ያስፈልግዎት ይሆናል።

ይህ ፕሮጀክት ቢያንስ በከፊል በ 'U.S. Department of Agriculture (በዩኤስ የግብርና ዲፓርትመንት) ን በተገኘ የፌደራል ፈንድ የተደገፈ ነው። የዚህ ሕትመት ይዘት የግድ የ U.S. Department of Agriculture (US የግብርና ዲፓርትመንት) ን አመለካከት ወይም ፖሊሲዎች የሚያንፀባርቅ አይደለም፣ ወይም የንግድ ስሞችን፣ የንግድ ምርቶችን ወይም ድርጅቶችን በአሜሪካ መንግሥት መፈቀዱን አያመለክትም።